ወይዛዝርት የተገኙበት፣ እኛም የምንወለድበት ነው፡፡ ባለመለከረው የትውልድ ቅድሚያ መሠረት ተራው የእሱ በመሆን አጽንተንለታል" የሚል ፍርድ በመስጠታቸው ሹመቱ ጸደቀለት፡፡

የጭቃ ሹምነት ማዕረግ በተቀበለበት ቀን የማዕረግ ልብስ ለብሶ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና የህዝብ አጀብ ክብር የተደረገለት ሲሆን እሱም ባህሉ የሚፈቅደውን ከፍተኛ ግብዣ በማዘጋጀት ህዝቡን አስተናገዱል፡፡ አባቴ በጭቃ ሹምነቱ ኃላፊነት ላይ ብዙም ሳይቆይ በ ፲፱፻፴፱ ዓ.ም. የካቲት ወር ላይ ዘውዴ ብርሃኑ የተባሉ የቅርብ ዘመዱን ምስለኔ አድርጎ በመሾም ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡

# ምዕራፍ ፫

# የሐዋርያዊ ተልዕኮ ጅማሬ ፲፱፻፴፱ - ፲፱፻፵፱

ቀርተዋል፡፡ ስለ አዲስ አበባ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መቃብር ቤት ቆይታው በሰጠው አንድ ቃለ መጠይቅ ላይ "... ወደ አገሬ ለመመለስ ሳስብና ስነሣ ድንገተኛ ሕመም ያመኛል፡፡ እንዲያውም በመጨረሻ በሕልሜ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት እጅና እግሬን በሰንሰለት አስረው የትም እትሄድም እዚሁ ሆነህ አገልግል እያሉ ሲገሥጹኝ በማየቴ ከዕንቅልፌ ነቅቼ ነገሩን ካለፉ ሁኔታዎች ጋር እያገናዘብኩ ሳሰላስለው በተለይም ከጐጃም ወደ አዲስ አበባ ስመጣ ደጌን (ደጀን) አፋፍ ላይ ባየሁት ሕልምና ለጸለይኩት ጸሎት የተሰጠኝ መልስ ይህ አዲስ አበባ የሚገኘው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ነው የሚለውን ሐሳብ በእምነት በመቀበል ከዚያ ጊዜ በኋላ ሙሉ ልቤን ሰብስቤ መንፈሳዊ ግልጋሎቴንም ትምህርቴንም መከታተል ቀጠልኩኝ..." በማለት ተናግሯል፡፡



## ኢትዮጵያ ሆይ! እኔ ክብርሽን ለሌላ አልሰጥም

ለከተማ ኑሮ አዲስ የነበረው አባቴ ከየካቲት ፲፱፻፴፱ ዓመተ ምሕረት እስከ ፲፱፻፵፪ ዓመተ ምሕረት ድረስ የነበሩትን ሦስት ዓመታት ያሳለፋቸው በአስተማሪነትና በተማሪነት ነው፡፡ ከቀኑ የተወሰነውን ሰዓት የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ቅኔ ሲያስተምር ይቆይና በተወሰነ ሰዓት ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየሄደ ይማር ነበረ፡፡

ከሁለቱ ዋነኛ ተግባሮች በተጨማሪ በዕድሜም ሆነ በዕውቀት ከሚበልጡት ሰዎች ጋር መወያየት፣ መጻሕፍትን ማጥናት፣ በጊዜው የነበሩ የሬዲዮና የጋዜጣ መረጃዎችን መከታተል ሥራዬ ብሎ የሚያዘወትራቸው ተግባራት ነበሩ፡፡ በተጨማሪም ሰዎችን በማግኘት መወያየትን እንደ አንድ የዕውቀት ማዳበሪያ ዘርፍ ይጠቀምበት ነበር፡፡ አዘውትሮ ከሚያገኛቸውና ጥልቅ የሆነ ትምህርትና ምክር ከሚገበይባቸው ሰዎች መካከል ከቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬና መምህር ይኄይስ ወርቁ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ዓይኑ ሥዉር እንደ መሆኑ መጠን ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስ የሚመራው፣ የዕለት ምግቡን የሚያዘጋጅለት፣ የልብሱንና መኖሪያ ክፍሉን ጽዳት የሚጠብቅለት ረዳት ያስፈልገው ነበር፡፡ በዚህ ረገድ እሱ ወደ አዲስ አበባ ከመጣ ኋላ ተከትለውት ከዲማ ከመጡ ዘመዶቹና ጓደኞቹ መካከል ባዩ እንየው፣ ፀዳሉ እድማሱ፣ መንግሥት ፈለቀ፣ አበበ የሥጋትና ሌሎችም በተሰያየ ጊዜ ዐብረውት እየኖሩ ይረዱት ነበር፡፡ በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ መኪኖች እንደ አሁኑ በርካታ ስላልነበሩ ብዙውን ጊዜ ያለ መሪ ይንቀሳቀስ እንደ ነበረም ነግሮኛል፡፡

ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የተሰጠውን ብሉያትን ከእነው ሊቃውንት መምህራን የማስቀረት ግዳጅ ለመወጣትና ዕውቀቱንም ለማዳበር ባደረገው ጥረት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ውስጥ መጽሐፈ ኢሳይያስን፣ መጽሐፈ ዐሥርቱ ወክልኤቱ ደቂቀ ነቢያትን፣ መጽሐፈ አስቴርንና መጽሐፈ ጦቢትን ከነሙሉ

"...በዛሬው ዓለም ያሉት አፈ ብልጦች እንደ መብዛታቸው መጠን የኢትዮጵያ መሬት በሌላው ክፍለ ዓለም የተዘረጋና ሰፊ መንግሥቷም በዚያው በኩል የተመሠረተ ቢሆን ኖሮ እኛ የዛሬዎቹ ወጣቶች ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ክብር ለመቀነስ የምናደርገውን ድካም ሌሎችም ሕዝቦች ስለ ሀገራቸው እድገት ሰፊ ታሪክ በመጻፍ የሚያደርጉትን ጥረት በማወዳደር ስንመለከተው ለጽሑፋቸው ማስደገፊያ ኢትዮጵያ የቆመችበትን የመሰለ ታሪክ መስላል ቢያገኙ ኖሮ እንኩዋን ሰውን የዕውቀት ሁሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን እናስረዳኸ ለማለት በሞከሩ ነበር፡፡..."[28]

አባቴ የሚያውቀውን ለማስተማርና ሊመጣ ይችላል ብሎ የሰጋበትን ጥፋት ለመከላከል ከእርሱ በማዕረግ፥ በዕውቀትና በዕድሜ የሚበልጡት ብቻ ይናገሩ ብሎ መጠበቅን አልወደደም፡፡ በዚህ ምክንያት የድርሻውን ለመወጣትና ወገኖቹን ለመቀስቀስ ዐቅሙ በቻለውና ባገኘው መድረክ ሁሉ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማያውቀውን ለማወቅና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ ለመገብየት በነበረው ጽኑ እምነት ምክንያት በቅድስት ሥላሴና በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከሚከታተለው፡የብሉያት ትምህርት በተጨማሪ በትርፍ ጊዜው ከክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬና ከመምህር ይኄይስ ወርቁ ጋር እየተገናኘ በትምህርቱና በተለያዩ ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ዕውቀት ለማግኘት ያደርግ የበረውን ጥረት አጥብቆ ቀጠለበት፡፡

በከፍተኛ ደረጃ የሚያስጨንቀውን የአዳዲስ እምነቶች ወረራ፥ የባህልና የታሪክ መበረዝ መከለስ ነገርንም አጥብቆ ይወያይበት ነበር፡፡ የአገሩን ታሪክ በአግባቡ ባለመማሩ ምክንያት የማንነት ቀውስ የጀማመረውን የዘመኑን ወጣት ትውልድ ለመታደግና ሊመጣ ይችላል ብሎ ከሩቅ ያየውን አገር አቀፋዊ ተግዳሮት ለመመከት በዐቅሙ እወጣቸዋለሁ ብሎ ያመነባቸውን የተለያዩ ዕቅዶች ነደፈ፡፡

[28] የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት



በዕውቀት ላይ ዕውቀትን እየጨመረ አገሩንና ቤተ ክርስቲያንን ወደ ማገልገል ግዳጅ እየገባ በነበረበት በዚያን ወቅት ይሰማው የነበረውን ስሜት እንደሚከተለው ገልጦታል፡፡

"...ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፥ ስለ ቀናችው ሃይማኖቷና ስለ ተቀደሰው ምግባሯ፥ በእግዚአብሔርና በእኔ መካከል ስላለውም ጥኑ ፍቅር፤ በኅሊናዬ የሚወጣው የሚወርደው ሐሳብ ያቃጥለኛል፡፡ ቆሜ፥ ተቀምጬ፥ ተኝቼ፥ ተነሥቼ በምሄድበትና በማርፍበት፥ በምበላበትና በምጠጣበት ጊዜ ሁሉ ትኩር አድርጌ የምመለከተው እሱኑ ብቻ ነው፡፡ ..."[29] ከላይ በተገለጠው ሁኔታ በተሰማው ቁጭትና ቅንዓት ምክንያት በግለሰብ ዐቅሙ ለመሥራት የነደፋቸው ዕቅዶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነበሩ፡፡

፩ኛ/ የእንግሊዘኛ ቋንቋና የብሬል ትምህርት መማር፥

፪ኛ/ በአዳዲስ እምነቶች እየተሳቡ ለነበሩ የኅብረተሰቡ አባላት በየሚገኙበት እየሄደ ትምህርት መስጠት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህራኖቻቸውን በይፋ በሚያገኝበት መድረክ ሁሉ በመሞገት ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው የኮበለሉ ወገኖች ጉዳዩን ተገንዝበው እንዲያመዛዝኑ መርዳት፤

፫ኛ/ በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት ላይ ከሚሰጠው ትምህርት በተጨማሪ በተለያዩ ማኅበራዊ ስብሰባዎች ላይ ትምህርት መስጠት፤

፬ኛ/ የመንግሥትም ሆነ የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት ችግሩን ችላ ብለው እንዳያዩት ማሳሰብና፤

፭ኛ/ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየእጁ ይዞ የሚያነባቸው መጻሕፍት ማዘጋጀት፥ ዋነኛ የትኩረትና የአካሄድ አቅጣጫዎቹ ነበሩ፤

[29] ዝኒ ከማሁ

ከሰፈር ሰፈር እየዞሩ ይህን ሥራ ይሠሩ በነበረበት ጊዜ ሁሉ "ይደክመዋል ብለህ ለእኔ እንዳታስብ አስፈላጊ በሚመስል ቦታ ሁሉ እየወሰድከኝ ችግሩን መቋቋም አለብን" በማለት አባቴ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ ለዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በሚሰማራበት ቦታ ሁሉ "ጳውሎስ" በተባለ ስም ይጠቀም ነበር፡፡ ለዚህ ሐዋርያዊ አገልግሎታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ "ጳውሎስ" የተባለ ስሙን ለመጀመሪያ ወንድ ልጁ መጠሪያነት ሰጥቶታል፡፡



# ምዕራፍ ፬

## ዘርፈ ብዙ የአገልግሎት ዘመናት
## ፲፱፻፶ - ፲፱፻፷፭